## የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴ ሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

## የባህል ፍርድ ቤቶችን ለማቋቋምና እውቅና ለመስጠት የሚያስችሉ መሰረታዊ መስፈርቶችን ለመደንገግ የወጣ ረቂቅ አዋጅ

### መግቢያ

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ መንግስት ለባህላዊ ተቋማት እና በባህላዊ መንገድ መዳኘትን እውቅና የሰጠ በመሆኑና ከመደበኛው ፍርድ ቤት ጎን ወደ ስራ የመግባታቸውን አስፈላጊነት የደነገገ በመሆኑ፤

የተለያዩ ግጭቶችን ለመፍታት ባህላዊ የግጭት መፍቻ ዘዴዎችን ማህበረሰቡ እየተጠቀመ በመሆኑ እና ይህንኑ በህግ እውቅና በመስጠት ማጠናከር መንግስት ሀላፊነት ያለበት መሆኑን በመገንዘብ፤

ባህላዊ ፍርድ ቤቶች ማህበረሰቡ ተደራሽ የፍትሕ አገልግሎት እንዲያገኝ፣ ቀለል ያለ ስነስርአት የሚከተሉ፣ ዘላቂ ሰላምን ለማስፈን የሚረዱ መሆኑን በመገንዘብ፤

እውቅና የሚሰጣቸው ባህላዊ ፍርድ ቤቶች በህገ መንግስቱ ላይ ከተደነገጉ የሰብዓዊ መብቶች እና ዲሞክራሲያዊ ፅንሰ ሀሳቦች ጋር የሚጣጣሙበት መስፈርቶችን መደንገግ በማስፈለጉ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ መንግስት አንቀጽ 55 ንዑስ አንቀጽ (1) እና አንቀጽ 78 ንዑስ አንቀጽ (5) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

### <u>ክፍል አንድ</u><br><u>ጠቅላላ ድንጋጌዎች</u>

**1. አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ "የባህል ፍርድ ቤቶችን ለማቋቋምና እውቅና ለመስጠት የሚያስችሉ መሰረታዊ መስፈርቶችን ለመደንገግ የወጣ አዋጅ ቁጥር………/2016" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡

## Federal Democratic Republic of Ethiopia

## A Draft Proclamation to Provide for the Fundamental Requirements for the Establishment and Recognition of Customary Courts in Ethiopia

### Preamble

Whereas the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia recognises customary institutions and calls for their establishment and operation as customary courts alongside formal courts.

Noting that Ethiopians frequently rely on customary dispute resolution mechanisms to settle various disputes and recognise that the government has the responsibility to provide legal recognition and strengthen this practice

Acknowledging that customary courts contribute to lasting peace, utilise simple procedures, and ensure community access to justice.

It is deemed essential to provide provisions that ensure their operation complies with the human rights principles and democratic aspirations of the constitution.

NOW, THEREFORE, in accordance with sub-Article (1) of Article 55 and sub-Article (5) of Article 78 of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows.

### <u>Part One</u><br><u>General Provisions</u>

**1. Short Title**

This Proclamation may be cited as 'Proclamation to Provide for the Fundamental Requirements for the Establishment and Recognition of Customary Courts, No. / 2024'.

## 2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፤

1. **"ህገ መንግስት"** ማለት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ መንግስት ነው፤
2. **"ባህላዊ ፍርድ ቤት"** ማለት በባህላዊ ሕጎች ላይ ተመርኩዞ አለመግባባቶችን ለመፍታት በፌደራል ወይም በክልል ሕጎች መሰረት የተቋቋመ ወይም እውቅና የተሰጠው አማራጭ ያለመግባባት መፍቻ ስርአት ነው፤
3. **"መደበኛ ፍርድ ቤት"** ማለት አግባብነት ባላቸው የፌደራል ወይም የክልል ሕጎች መሰረት የተቋቋመ የመጀመሪያ ደረጃ፣ ከፍተኛ እና ጠቅላይ ፍርድ ቤት ማለት ነው፤
4. **"የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት"** ማለት የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ወይም የክልል ወረዳ ፍርድ ቤት ማለት ነው፤
5. **"ሀይማኖታዊ ፍርድ ቤት"** ማለት በሀይማኖታዊ ስርአት መሰረት አለመግባባቶችን ለመፍታት በፌደራል ወይም በክልል ሕጎች መሰረት የተቋቋመ ፍርድ ቤት ነው፤
6. **"ክልል"** ማለት በህገ መንግስት አንቀፅ 47 የተመለከተው ማንኛውም ክልል ሲሆን የአዲስ አበባና የድሬዳዋ ከተሞች አስተዳደሮች ይጨምራል፤
7. **"ምክር ቤት"** ማለት በዚህ አዋጅ <u>የተቋቋመ</u> የፌደራል ወይም የክልል የባህላዊ ፍርድ ቤቶች አስተዳደር ምክር ቤት ነው፤

## 2. Definitions

In this Proclamation, unless the context provides otherwise:

1. "**Constitution**" the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, Proclamation No. 1/1995.
2. "**Customary Courts**" means courts established or social institutions recognised in accordance with the provisions of regional or federal laws to adjudicate disputes based on customary laws.
3. "**Regular Courts**" means the First instance, High and Supreme Courts established under relevant federal and regional laws.
4. "**First instance court**" means the federal first instance court or regional Wored level court.
5. "**Religious Courts**" means a court established by the provisions of regional or federal laws to adjudicate disputes based on religious laws.
6. "**Regions**" means regional states and city administrations recognised in Ethiopia.
7. "**Council**" means federal or regional customary courts administration council established under this proclamation.

8. **"የባህል ተቋም"** ማለት የባህል ሕግንና የህዝቡን እሴቶች መሠረት አድርጎ አለመግባባትን የሚፈታና ዕርቅን የሚያወርድ በአካባቢው ህብረተሰብ ዘንድ እንደ ተቋም የሚታወቅ እና የራሱ ስርዓትና አሰራር ያለው ማለት ነው፤
9. **"የባህል ህግ"** ማለት ባህላዊ ፍርድ ቤት ወይም ተቋማቱ የሚሰሩበት የአሰራር ስርአት ነው፤
10. **"ሽማግሌ"** ማለት በማህበረሰቡ ባህላዊ ስርዓት ተመርጦ በባህላዊ ፍርድ ቤቶች የዳኝነትና መሰል ጉዳዮችን የሚያከናውን ሰው ሆኖ እንደየአካባቢው የባህል ህግ የተለያዩ ስያሜዎች ሊጠራ ይችላል፤
11. **"ባለጉዳይ"** ማለት በባህላዊ ፍርድ ቤት ተከራካሪ፣ ባለጉዳይ፣ ተሸማጋይ፣ ከሳሽ፣ ተከሳሽ፣ ይግባኝ ባይ፣ መልስ ሰጪ የሆነ ሰው ነው፤
12. **"ሰው"** ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤
13. ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለፀው የሴትንም ያካትታል፡፡

### 3. የተፈፃሚነት ወሰን

ይህ አዋጅ በፌዴራልና በክልል የሚቋቋሙ ወይም እውቅና የሚሰጣቸው ባህላዊ ፍርድ ቤቶች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

8. **"Customary institution"** means an institution that works on the settlement of disputes and reconciliation on the basis of customary law and societal values recognised by society as an institution and that has its own working system and procedures.
9. **"Customary law"** means a set of rules and practices that customary courts and institutions apply.
10. **"Elder"** means a person selected according to relevant customary practices to adjudicate disputes in customary courts and may be known by other names depending on the applicable customary rules.
11. **"Client"** means a person that appears before the customary court as an applicant, respondent, appellant or participant in mediation or reconciliation.
12. **"Person"** means a natural or juridical person.
13. Any expression in the masculine gender includes the feminine.

### 3. Scope of Application

This proclamation applies to customary courts established or recognised at federal and regional levels.

## ክፍል ሁለት
## አላማ፣ መርሆች፣ ጥበቃ

**4. ዓላማ**

አዋጁ የሚከተሉት አላማዎች አሉት:-

1. የባህላዊ ፍርድ ቤቶች ሲቋቋሙ፣ እውቅና ሲሰጣቸው ወይም ተግባራቸውን ሲያከናውኑ የሰብዓዊ መብቶች እና ዲሞክራሲያዊ ድንጋጌዎችን በማይጻረር እና ባከበረ መልኩ እንዲሆን አቅጣጫ የሚሰጡ ጠቅላላ ድንጋጌዎችን ማስቀመጥ፤
2. የባህላዊ ፍርድ ቤቶች ውጤታማ አሰራር እንዲኖራቸው ማመቻቸት፣ ውሳኔም ተቀባይነት እንዲያገኝና ተፈጻሚነት እንዲኖረው ማድረግ፤
3. የባህላዊ ፍርድ ቤቶች ሲቋቋሙ፣ እውቅና ሲሰጣቸው ወይም ተግባራቸውን ሲያከናውኑ የየባህላዊ ተቋማቱን ልዩ ገጽታዎች የማስጠበቁ አስፈላጊነት እንደተጠበቀ ሆኖ የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች የተከተሉ እንዲሆኑ ማድረግ፤
4. ባህላዊ የሙግት መፍቻ እሴቶችና ስርአቶችን መጠበቅና ማበረታታት፡፡

**5. መሰረታዊ መርሆች**

የባህላዊ ፍርድ ቤቶች መቋቋም፣ እውቅና አሰጣጥ እና አሰራር በሚከተሉት መርሆዎች ይመራል:-

1. **ፍቃድ ላይ የተመሰረተ እና አማራጭ ስለመሆናቸው፤**

   ሀ/ የባህላዊ ፍርድ ቤቶች እንደ አማራጭ የግጭት እና አለመግባባት መፍቻ ዘዴዎች ሆነው ከመደበኛ ፍርድ ቤቶች ጎን ለጎን ያገለግላሉ፤



## Part Two
## Purpose, principles and guarantees

**4. Purpose**

This law has the following objectives:

1. Providing general provisions that ensure the establishment and operation of customary courts are compliant with the human rights and democratic principles enshrined in the Constitution.
1. Facilitating the effective operation of customary courts and promoting the acceptance and enforcement of their decisions.
2. Without prejudice to the need to maintain regional specificities, ensuring that the establishment and operation of customary courts, mirror the provisions of the provisions provided in this law.
3. Safeguarding and promoting customary values and institutions of dispute resolution

**5. Basic Principles**

The establishment, recognition and operation of customary courts shall be based on the following principles:

1. **Consent-based and Alternative**

   i. Customary courts function alongside the regular courts as alternative avenues of dispute resolution

ለ/ ማንም ሰው ካለፍቃዱ በባህላዊ ፍርድ ቤቶች ሊዳኝ አይችልም፡፡

2. **ባህላዊ ስርአቱ ላይ ጉዳት ያለማድረስ፣**

በዚህ አዋጅ የተመለከቱ አስገዳጅ መስፈርቶች እንደተጠበቁ ሆነው የባህላዊ ፍርድ ቤቶች ማቋቋሚያ እና እውቅና መስጫ ሂዳት የባህላዊ ተቋማትን እና አሰራሮችን ተዓማኒነት እና ባህላዊ ዕሴቶችን ባስጠበቀ መልኩ መመስረት ይኖርባቸዋል፡፡

3. **የሰብዓዊ መብት ጥበቃዎች፣**

ሀ/ በባህላዊ ፍርድ ቤቶች የሚፈፀሙ ሥነ ሥርዓቶች በሙሉ የባለጉዳይ ወገኖችን ሰብዓዊ መብት ያከበሩ መሆን አለባቸው፡፡

ለ/ ባህላዊ ፍርድ ቤቶች የሰዎችን ማህበራዊ ሁኔታ፣ ዘር፣ ብሔር፣ ዜግነት፣ ማህበራዊ መገኛ፣ የቆዳ ቀለም፣ ቋንቋ፣ ሀይማኖት፣ ፖለቲካዊ ወይም ሌላ ዕሳቤ፣ ሀብት፣ ትውልድ፣ አካል ጉዳት ወይም ሌላ ደረጃ ላይ ከተመሰረተ አድልዕዎ ነፃ በሆነ መልኩ መዳኘት እና አገልግሎት መስጠት አለባቸው፡፡

ሐ/ ሴቶች እና ወንዶች በባህላዊ ፍርድ ቤቶች በእኩልነት መስተናገድ አለባቸው፡፡

መ/ ባህላዊ ፍርድ ቤቶች የህፃናትን የቀደምትነት ጥቅም የሚያረጋግጡ መሆን አለባቸው፡፡



ii. No person shall be compelled to the jurisdiction of customary courts.

2. **The Principle of No Harm**

Without prejudice to the mandatory provisions of this law, the process of establishing and recognizing customary courts must ensure the preservation of the integrity and traditional values of customary institutions.

3. **Human Rights Guarantees**

i. Proceedings before Customary Courts shall respect the human rights of the parties.

ii. Customary courts shall adjudicate cases without discrimination as regards persons, social conditions, race, nation, nationality, social origin, colour, sex, language, religion, political or other opinion, property, birth or other status.

iii. Women and Men shall be treated equally before customary courts.

iv. Customary Courts shall ensure that the best interest of the child is respected.

The Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Justice

ሠ/ ባህላዊ ፍርድ ቤት የሚቀርቡ ባለጉዳዮች ወገኖች አስተርጓሚ ይዘው የመቅረብ መብታቸው የተጠበቀ ነው።

ረ/ በባህላዊ ፍርድ ቤቶች የሚተላለፉ የቅጣት ውሳኔዎች አካላዊ ቅጣትን ጨምሮ ኢሰብዓዊ፣ ጭካኔን የተሞሉ ወይም አወራጅና ክብረ ነክ መሆን የለባቸውም::

ሰ/ በፍርድ አሰጣጥ ሥነ ሥርዓት ሂደት ወቅት በባህላዊ ፍርድ ቤቶች የተፈፀመ የሰብዓዊ መብት ጥሰት ይግባኝ የመጠየቂያ በቂ ምክንያት መሆን ይችላል::

ቀ/ ባህላዊ ፍርድ ቤቶች እንደ ምስክሮችን ማሰማት ወይም ማስረጃዎች ማቅረብን የመሰሉ የሥነ ሥርዓት ጉዳዮችን በሚመለከት ለመደበኛ ፍርድ ቤቶች የተደነገጉ የወንጀልም ሆነ የፍትሀ ብሔር ሥነ ሥርዓቶችን እንዲከተሉ አይገደዱም::

በ/ በባህላዊ ፍርድ ቤቶች የሚወሰኑ ወይም የሚተገበሩ የጉዳት ካሳ ወይም ሌሎች ማናቸውም የእርማት እርምጃዎች ከየትኛውም ዓይነት አድልዕዎ የፀዱ መሆን ይኖርባቸዋል::

4. **ተደራሽነት**

ባህላዊ ፍርድ ቤቶች ማህበረሰቡ በሚገኝበት እና አገልግሎቱ ተደራሽ በሚሆንበት አግባብ እንዲደራጁ እና እውቅና እንዲሰጣቸው መደረግ አለበት::

v. Women and Men shall be treated equally before customary courts.

vi. Parties shall have the right to appear before customary courts with the help of an interpreter.

vii. Sanctions by customary courts shall not constitute any form of inhuman or degrading treatment, including corporal punishment.

viii. A violation of human rights guarantees in customary court proceedings shall constitute a ground for appeal.

ix. Proceedings before customary courts are not required to adopt procedures used in criminal or civil proceedings in regular courts, such as the hearing of witnesses or the presentation of evidence.

x. Determination of compensations or other forms of redress by customary courts shall not be carried out in a manner that is discriminatory based on any ground.

4. **Accessibility**

Customary courts shall be recognized and established in a manner that takes into account their accessibility to the community

## ክፍል ሶስት
## የባህል ፍርድ ቤት እውቅና አሰጣጥና አደረጃጀት

### 6. የባህል ፍርድ ቤቶች እውቅና አሰጣጥ

1. የባህል ተቋማት እንደ ባህላዊ ፍርድ ቤት እውቅና ለማግኘት መመዝገብ ይኖርባቸዋል።

2. የምዝገባና የእውቅና አሰጣጥ ዝርዝር መስፈርቶች እንደየእውቅና ሰጪው አካል የሚወሰን መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ የሚከተሉትን ዋና ዋና መስፈርቶች ማሟላት ይኖርበታል።

ሀ/የባህል ተቋሙ አለመግባባቶችና ግጭቶችን ለመፍታት የሚያስችል አደረጃጀት ያለው መሆኑ፤

ለ) የባህል ተቋሙ እውቅና ለማግኘት ፍላጎት ላይ የተመሰረተ ጥያቄ ስለመቅረቡ መረጋገጡ፤

ሐ) የባህል ተቋሙ በዚህ አዋጅ የተቀመጡትና አላማዎችና መርሆዎችን ለመከተል ፍቃደኛ መሆኑን የገለጸ መሆኑ::

## Part Three
## Recognition and Licensing of Customary Institutions

### 6 Recognition of Customary Courts

1. Customary institutions shall be registered in order to operate as customary courts.

2. Notwithstanding detailed registration conditions that shall be determined by the registration and licensing body, the following main requirements must be fulfilled at all times.

   i. The institution has a structure that facilitates disputes or conflict resolution
   ii. The institution has submitted a voluntary request for recognition as a customary court.
   iii. The institution has expressed its commitment to adhere to the principles and guarantees established in this law.

7. **ምዝገባን ስለ መሰረዝ**

1. ተቋሙ በዚህ አዋጅ የተደነገጉ መሰረታዊ መርሆዎችንና መስፈርቶች በተደጋጋሚ ሳያከብር ሲቀር እውቅና ሰጪው አካል ለባህላዊ ፍርድ ቤቶች የሰጠውን እውቅና ሊሰርዝ ይችላል።
2. በዚህ አንቀጽ መሰረት የባህላዊ ፍርድ ቤት ምዝገባ ሲሰረዝ የተሰረዘበትን ምክንያት በግልፅ ማስቀመጥ ይኖርበታል።
3. እውቅናው የተሰረዘ የባህል ተቋም በዚህ አዋጅ የተደነገጉ መስፈርቶችን በማሟላት እንደ ባህላዊ ፍርድ ቤት ለማገልገል በድጋሚ ለመመዝገብ ጥያቄ ሊያቀርብ ይችላል።

**<u>ክፍል አራት</u>**

**<u>የባህል ፍርድ ቤት የሽማግሌዎች ሹመት እና ከሹመት ስለመነሳት</u>**

8. የባህላዊ ፍርድ ቤት ሽማግሌዎች ሹመት እና ከሹመት መነሳት በባህላዊ ስርዓቱ መሰረት ይሆናል።
9. የባህላዊ ፍርድ ቤት ሽማግሌዎች ሹመት የሴቶችን ተዋጽኦ ያረጋገጠ መሆን ይኖርበታል።
10. ወንጀለኛ ተብሎ በፍርድ ቤት ውሳኔ የተላለፈበት ሰው ወይም የፖለቲካ ፓርቲ አባል የሆነ ሰው ወይም የአዕምሮ ውስንነት ያለበት ሰው የባህላዊ ፍርድ ቤቶች ዳኛ ሆኖ ሊሾም አይችልም፡፡
11. የባህላዊ ፍርድ ቤት ዳኞች በገዛ ፈቃዳቸው ከሹመታቸው ለመልቀቅ ወይም ከፊታቸው ከቀረበ ጉዳይ ላይ ብቻ ራሳቸውን ለማግለል ይችላሉ፡፡
12. ባህላዊ ፍርድ ቤቶች ተጠባባቂ ወይም አማራጭ ዳኛ ሊኖራቸው ይገባል፡፡
13. የባህላዊ ፍርድ ቤቶችን ለመመስረት በወጡ ህጎች ላይ ተለይተው ከተዘረዘሩ ምክንያቶች ውጭ በሌላ በማናቸውም ምክንያቶች የባህላዊ ፍርድ ቤት ዳኞች ሊሻሩ አይችሉም ፡፡

7. **Revocation of Registration**

1. A licensing body may revoke the registration and license granted to customary institutions if the institutions repeatedly fail to comply with the stipulations of this law.
2. The decision to revocation of license reached under this provision shall provide clear reasons for such revocation.
3. Customary institutions whose licenses have been revoked may reapply for registration by implementing measures that guarantee their compliance with this law if granted re-registration

**<u>Part Four</u>**

**<u>Appointment and Termination of Customary Court Judges</u>**

8. The Appointment and termination of customary court judges shall be guided by the relevant customary practice.
9. The appointment of customary court judges shall ensure the inclusion of female judges.
10. A person with a criminal record, or is a member of any political party or is mentally impaired shall not serve as a judge in customary courts.
11. Customary court judges have the right to recuse themselves from a particular case or resign as judges.
12. Customary courts shall have reserve or alternative judges.
13. Customary Court judges shall not be terminated for reasons other than specified in laws establishing customary courts.

## ክፍል አምስት
## የባህላዊ ፍርድ ቤቶች መሠረታዊ መዋቅር

14. ባህላዊ ፍርድ ቤቶች የመጀመሪያ እና የይግባኝ ሰሚ ችሎቶችን የያዘ ባለሁለት እርከን መዋቅር ይኖራቸዋል፡፡
15. በቀበሌ ደረጃ የሚኖረው ባህላዊ ፍርድ ቤት የመጀመሪያ ደረጃ የባህላዊ ፍርድ ቤት ይሆናል፡፡
16. በወረዳ ደረጃ የሚኖረው ባህላዊ ፍርድ ቤት የይግባኝ ሰሚ የባህላዊ ፍርድ ቤት ይሆናል፡፡
17. ባህላዊ ፍርድ ቤቶች ከመደበኛው ፍርድ ቤቶች ጋር የሚመሳሰሉ የችሎት ክፍሎች እንዲኖራቸው አይጠበቅባቸውም፡፡
18. በቀበሌ ደረጃ የሚኖሩ ባህላዊ ፍርድ ቤቶች እንደአመቺነቱ በአካባቢያቸው የሚገኙ ባህላዊ ይዞታዎችንና ቦታዎችን የቀረበላቸውን ጉዳይ ለመቀበል፣ ለመስማትና ለመወሰን እንደ የችሎት ቦታዎች ሊጠቀሙባቸው ይችላሉ፡፡

## ክፍል ስድስት
## የዳኝነት ስልጣን

### 19. የፍሬ ነገር የዳኝነት ስልጣን

ባህላዊ ፍርድ ቤቶች በሚከተሉት ጉዳዮች ላይ የፍሬ ነገር ስልጣን ይኖራቸዋል፡-

1. በቤተሰባዊ እና ግለሰባዊ ጉዳዮች፤
2. በግል አቤቱታ የሚያስቀጡ ወንጀሎች እና የደንብ መተላለፍ ወንጀሎች፤
3. በሌሎች ሕጎች ላይ በግልጽ ተለይተው የማየት እና የመወሰን ስልጣን በተሰጣቸው ጉዳዮች ላይ አይቶ የመወሰን ስልጣን አላቸው፡፡
4. በግል አቤቱታ በሚታዩ ወንጀሎች ጉዳይ በባህላዊ ፍርድ ቤቶች የተጀመረ ክስ ወይንም ችሎት ማንኛውንም የፖሊስ ወይንም የግል ምርመራ ያቋርጣል

## Part Five
## Basic Structure of Customary Courts

14. Customary Courts shall have two-tiered structures with primary and appellate jurisdiction.
15. Kebele-level customary courts shall be the Primary or First Instance Customary Courts.
16. Woreda-level customary courts shall serve as Appellate Customary Courts
17. Customary courts are not required to operate in a courtroom similar to that of the regular courts.
18. Kebele-level customary courts may use traditional locations and places to hear cases before them.

## Part Six
## Jurisdiction

### 19. Subject Matter Jurisdiction

customary courts shall have subject matter jurisdiction over:

1. family and personal matters
2. petty offences and crimes punishable only upon complaint
3. matters expressly reserved to fall under their jurisdiction pursuant to other applicable laws
4. For crimes punishable upon complaint, proceedings before customary courts shall bar any ongoing private or police investigation.

The Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Justice

## 20. የአስማሚነት የዳኝነት ስልጣን

1. ባህላዊ ፍርድ ቤቶች ከመደበኛ ፍርድ ቤቶች ለሽምግልና ወይም ለግልግል የሚላኩላቸው ጉዳዮች ላይ የአስማሚነት ሚና ይኖራቸዋል፡
2. የተላከው የሽምግልና ወይም የግልግል ጥያቄ የሽምግልናው ወይም የግልግሉን ወሰን እና የጊዜ ገደብ በሚመለከት ልዩ መመሪያዎችን ማካተት ይኖርበታል፡፡
3. መደበኛው ፍርድ ቤት አንድን ጉዳዩ ወደ ባህላዊ ፍርድ ቤት ከመራው ሁሉም ወገኖች ፈቃድ እንደሰጡ የሚቆጠር ሲሆን ይህንን ፈቃድ ማንሳት አይቻልም፡፡
4. ከውሳኔው ለመውጣት አስገዳጅ ሁኔታዎች ካልተገኙ በቀር በባህላዊ ፍርድ ቤቶች የተሰጠን የሽምግልና ወይም የግልግል ውሳኔን መደበኛ ፍርድ ቤቶች ማክበር ይኖርባቸዋል፡፡

## 21. የማስታረቅ የዳኝነት ስልጣን

1. በየፍሬ ነገር ስልጣናቸው ስር ከተደነገገው በተጨማሪ በሌሎች በወንጀል ጉዳዮች ላይ ባህላዊ ፍርድ ቤቶች ወንጀል ፈጻሚዎችን እና የግል ተበዳዮችን ማስታረቅን በሚመለት የዳኝነት ስልጣን ሊኖራቸው ይችላል፡፡
2. የማስታረቅ የዳኝነት ስልጣን ጥያቄ በባህላዊ ፍርድ ቤቱ፣ በግል ተበዳይ፣ በወንጀል ፈጻሚው፣ በወንጀል ፈጻሚው ወይም በግል ተበዳይ ዘመድ አዝማድ ወይም በማናቸውም ሶስተኛ ወገኖች ሊቀርብ ይችላል።
3. ከላይ የተደነገገው ቢኖርም የባህላዊ ፍርድ ቤቶች የማስታረቅ የዳኝነት ስልጣን በመደበኛ ፍርድ ቤቶች የሚኖር የወንጀል ክስ ሂደትን አያስቀርም።
4. በባህላዊ ፍርድ ቤቶች የተደረገ ውጤታማ የእርቅ ሂደት አግባብነት ባላቸው ሕጎች መሰረት እንደ ቅጣት ማቅለያ ሊወሰድ ይችላል፡፡
5. የማስታረቅ ሂደት ባለጉዳዮች ፈቃዳቸውን ሳይሰጡ ሊጀመር አይችልም፡፡

## 20. Referral Jurisdiction

1. Customary Courts shall exercise jurisdiction over cases referred to them for arbitration or mediation by regular courts.
2. The arbitration or mediation referral shall include specific instructions on the scope and timeline of the requested arbitration or mediation.
3. A regular court's referral of a case to Customary Courts shall be considered as fulfilling the requirement of consent, and this consent may not be withdrawn
4. Regular courts are bound to uphold mediation or arbitration decisions by Customary Courts unless and otherwise there are compelling reasons to deviate from such decisions.

## 21. Reconciliatory Jurisdiction

1. Customary Courts may have jurisdiction over criminal cases other than those listed under their subject matter jurisdiction with the sole purpose of reconciling victims and offenders.
2. Reconciliatory jurisdiction may be initiated by Customary Court Judges, the victim, the perpetrator, families or relatives of the victims or offenders, or a third party.
3. Notwithstanding the preceding stipulations, the exercise of reconciliatory jurisdiction by customary courts shall not bar or discontinue a criminal proceeding before the regular courts.
4. Effective reconciliation by customary courts may be used as a mitigating factor by regular courts in accordance with applicable laws.
5. Reconciliation proceedings shall not commence without the consent of the alleged offender.

6. የእርቅ ሂደቱ የወንጀል ፈጻሚው ባቀረበው ጥያቄ መሠረት የተጀመረ ከሆነና ወንጀል ፈጻሚው እውነተኛ የመፀፀት ስሜት ካሳየ የእርቅ ሂደቱ ውጤት ምንም ይሁን የእርቅ ሂደቱን የያዘው ባህላዊ ፍርድ ቤት የወንጀል ጉዳዩን ለሚመለከተው መደበኛ ፍርድ ቤት የወንጀል ፈጻሚውን ቅጣት እንዲያቀልለት አስተያየቱን ሊያቅርብ ይችላል፡፡
7. በዚህ አንቀጽ ላይ ለተደነገገው አፈጻጸም ሲባል የባህላዊ ፍርድ ቤት ዳኞች ወይም ተወካዮቻቸው በጥበቃ ስር የሚገኙ ሰዎችን መጎብኘት ይችላሉ፡፡
8. የእርቅ ሂደት ላይ የተገለጹ ማናቸውም ጉዳዮች በመደበኛ ፍርድ ቤቶች የተከሳሽን ጥፋተኝነት ለማስረዳት በማስረጃነት መቅረብ አይችሉም።
9. ባህላዊ ፍርድ ቤቶች የማስታረቅ የዳኝነት ስልጣን ባላቸው ጉዳዮች ላይ ውጤታማ የእርቅ ሂደት ከተገኘ ዐቃቤ ሕግ በመደበኛ ፍርድ ቤት በመታየት ላይ ያለውን የወንጀል ክስ በልዩ ሁኔታ ሊያቋርጥ ይችላል፡፡

## 22. ይቅርታን የማመቻቸት የዳኝነት ስልጣን

1) ባህላዊ ፍርድ ቤቶች በጥፋተኞች ወይም ወንጀለኞች እና በተበዳዮች ወይም ሕዝብ መካከል የሚኖር የይቅርታ ስነ ሥርዓት ማመቻቸት ይችላሉ፡፡
2) አግባብነት ባላቸው ሕጎች መሠረት መደበኛ ፍርድ ቤቶች ሕዝብን ይቅርታ መጠየቅን እንደ ቅጣት በሚያስተላልፉበት ጊዜ ባህላዊ ፍርድ ቤቶች ይቅርታውን እንዲያስፈፅሙ ሊጠይቁ ይችላሉ፡፡
3) በዚህ አንቀጽ ላይ ለተደነገገው አፈጻጸም ሲባል የባህላዊ ፍርድ ቤት ዳኞች ወይም ተወካዮቻቸው የወንጀል ፍርደኞችን መጎብኘት ይችላሉ፡፡

6. Provided that the offender initiated a reconciliatory jurisdiction, Customary Courts may recommend that regular criminal courts mitigate a sentence, regardless of the outcome of reconciliation proceedings, if the offender has shown a sincere sense of remorse.
7. For purposes of this article, customary court judges or their representatives have the right to visit persons held in custody.
8. Reconciliation proceedings shall not be used as evidence of wrongdoing against the defendant before the regular courts.
9. In the event of effective reconciliation, the prosecutor may exceptionally decide not to pursue a criminal case using its regular courts on matters that gave rise to the reconciliatory jurisdiction of customary courts.

## 22. Jurisdiction to Facilitate Apology

1. Customary Courts may facilitate the offer and acceptance of apology between the offender or convict and the victims or the public.
2. Regular Courts may request customary courts to facilitate the enforcement of public apology as a secondary punishment in cases where they impose it in accordance with the relevant criminal laws.
3. For purposes of this article, customary court judges or their representatives may visit persons imprisoned after conviction.

### 23. የዳኝነት ስልጣን አለመኖር

ባህላዊ ፍርድ ቤቶች በሚከተሉት ጉዳዮች ላይ የመዳኘት ስልጣን አይኖራቸውም:-

1. በሌሎች ህጎች በተለየ ሁኔታ ካልተደነገገ በስተቀር የእስራት ቅጣት ቀሪ የማይደረግባቸው ወንጀሎችን በሚመለከት፤
2. በከስ አቅራቢነት በሚታዩ ወይም ተጎጂ ግለሰብ የሌለባቸው ወንጀሎች እና ደንብ መተላለፍ ጉዳዮች፤
3. በግል አቤቱታ በሚታዩ ወንጀል ወይም የደንብ መተላለፍ ጉዳዮች በባህላዊ ፍርድ ቤት እየታየ መሆኑ ከታወቀ በፖሊስ የተጀመረ ምርመራ ይቋረጣል፤
4. መንግስትን፣ የመንግስት ተቋማትን የሚመለከቱ፣ በከስ አቅራቢነት ብቻ የሚሰሙ የደንብ መተላለፍ ወንጀሎች፤
5. ለመደበኛ ፍርድ ቤት ቀርቦ በመታየት ላይ ያለ ጉዳይ፤
6. ከላይ የተደነገገው ቢኖርም ሁሉም ተከራካሪ ወገኖች ተስማምተው መደበኛ ፍርድቤቱ ጉዳያቸውን ወደ ባህላዊ ፍርድ ቤት እንዲመራላቸው መጠየቅ ይችላሉ::
7. የክልል ወይም የፌደራል መንግስትን በቀጥታ በሚመለከቱ ጉዳዮች::

## ክፍል ሰባት
## የባህላዊ ፍርድ ቤት የዳኝነት አካሄድ

### 24. የተከራካሪ ወገኖች ቃድ

1. ባህላዊ ፍርድ ቤቶች ጉዳዩን በነሱ የማየትና የመወሰን ፈቃድ ያልሰጠ ሰውን ወይም ያካተተ ጉዳይን መመልከት አይችሉም::

### 23. Lack of Jurisdiction

Customary courts shall not have jurisdiction over the following matters:

1. Unless otherwise expressly provided under other laws, customary courts may not have jurisdiction over offences punishable only by a term of imprisonment.
2. Customary courts may not have jurisdiction over offences in which there is no direct individual victim or to which the prosecutor is a party.
3. For crimes punishable upon complaint, proceedings before customary courts shall bar any ongoing investigation by the police.
4. Customary courts shall not have jurisdiction over petty offences involving the government and its institutions or cases to which the police or the prosecutor is a party.
5. Customary courts shall not have jurisdiction over cases pending before the regular courts.
6. Notwithstanding the preceding provision, disputing parties may unanimously request regular courts to refer their cases to Customary Courts.
7. Customary courts shall not have jurisdiction over disputes in which the local or federal government is a party.

## Part Seven
## Proceedings Before Customary Courts

### 24. Consent of the Parties

1. Customary courts shall not see cases involving an individual or entity not consented to their jurisdiction.

2. ፈቃድ ከማናቸውም ፍራቻ፣ ተጽዕኖ ወይም ዛቻ ነጻ በሆነና በማያሻማ ሁኔታ መገለጽ ይኖርበታል፡፡
3. ፈቃድ በቃል፣ በምልክት ቋንቋ ወይም በጽሁፍ ሊገለጽ ይችላል፣
4. በባህላዊ ፍርድ ቤት መቅረብ ብቻውን ፈቃድ እንደመስጠት አይቆጠርም፡፡
5. የባህላዊ ዳኝነት ሥነ ሥርዓት ከተጀመረ በኋላ ቀድሞ የተሰጠ ፈቃድን ማንሳት አይቻልም፡፡
6. ለዚህ ድንጋጌ ዓላማ ክርክር ለመስማት ቀጠሮ መስጠት የባህላዊ ዳኝነት ሥነ ሥርአት ሂደት መጀመሩን ያመላክታል፡፡

## 25. ይርጋ

ይርጋን በተመለከተ አግባብነት ባላቸው ሕጎች የተደነገጉ የጊዜ ገደቦች ወይም የይርጋ ድንጋጌዎች የባህላዊ ፍርድ ቤቶች የዳኝነት ስልጣን ላይ ተፈጻሚነት አይኖራቸውም፡፡

## 26. ውሳኔ ስላገኙ ጉዳዮች

1. በአንድ ባህላዊ ወይም ሀይማኖታዊ ፍርድ ቤት ታይቶ ውሳኔ ባገኘ ጉዳይ ላይ ተመሳሳይ ባለጉዳይ ይህንኑ ጉዳይ በሌላ ባህላዊ ወይም ሀይማኖታዊ ፍርድ ቤት ወይም በመደበኛ ፍርድ ቤት በድጋሚ ለማቅረብ አይችልም፡፡
2. በመደበኛ ፍርድ ቤት ታይቶ ውሳኔ ባገኘ ጉዳይ ላይ ተመሳሳይ ባለጉዳይ ይህንኑ ጉዳይ በባህላዊ ፍርድ ቤት በድጋሚ ለማቅረብ የተከለከለ ነው፡፡

2. Consent shall be given unequivocally, free from any form of fear, influence, or intimidation.
3. Consent may be given either verbally, in sign language, or in writing.
4. Appearance before the Customary Court shall not in itself constitute giving of consent.
5. Consent shall not be withdrawn once customary proceedings have started.
6. For purposes of this Article, scheduling of a hearing amounts to the commencement of customary proceedings.

## 25. Temporal Jurisdiction

The jurisdiction of Customary Courts shall not be subjected to the period of limitations as prescribed under other laws.

## 26. Resolved Cases

1. A case that has received a final decision from a customary court shall not be brought before any other customary court, religious court, or regular court.

2. It is prohibited for the same person to bring before a customary court a case that has already received a final decision from either a religious or a regular court.

## 27. የባህላዊ ዳኝነት ስራ ስለሚከናወንበት ስፍራ

የባህላዊ ዳኝነት ሚከናወንበት ስፍራ እንደየ ባህሉ ስርአት የሚወሰን ይሆናል።

## 28. በባህላዊ ዳኝነት ተፈፃሚ ስለሚደረግ ህግ

1. የባህል ፍርድ ቤት ተፈፃሚ የሚያደርገው የሚመራበትን የባህል ህግ ይሆናል።
2. ባህላዊ ፍርድ ቤቶች ማስረጃ የማቅረብና እና የሥነ ሥርዓት ጉዳዮችን በሚመለከት መደበኛውን የወንጀልም ሆነ የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ህጎች እንዲከተሉ አይገደዱም፡፡

## 29. ስለ ይግባኝ

1. ባህላዊ ስርዓቶች በይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ደረጃ እውቅና አግኝተው እንዲደራጁ ይደረጋል።
2. የባህላዊ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት በየመጀመሪያ ደረጃ ባህላዊ ፍርድ ቤት ውሳኔ ላይ የመጨረሻ ይግባኝ የማየት ስልጣን አለው፡፡
3. የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ባህላዊ ፍርድ ቤት በተሰጠ ውሳኔ ላይ ከመሰረታዊ የሰብአዊ መብት መርሆዎችና በዚህ አዋጅ ከተመለከቱ ስርአቶች አንፃር በይግባኝ አይቶ የመጨረሻ ውሳኔ የመስጠት ስልጣን አለው፡፡
4. በተለይ በመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በሚቀርብ ይግባኝ አቅም የሌላቸው ሴቶች፣ ህፃናትና አካል ጉዳተኞች ነፃ የህግ ድጋፍ የሚያገኙበት ሁኔታ መመቻቸት አለበት፡፡



## 27. The Seat of Customary Court

The place and location of a customary court shall be determined in accordance with the applicable customary system.

## 28. Law applicable in customary justice

1. Customary courts shall apply customary laws applicable to them
2. Customary courts shall not be required to adopt procedures in criminal or civil proceedings similar to those of the regular courts, including the hearing of witnesses or the presentation of evidence.

## 29. Appeal

1. Customary Courts shall be recognized and established at the appellate level.
2. The customary appellate court shall hold final appellate jurisdiction over the decisions rendered by primary customary courts.
3. The regular first-instance court shall hold final appellate jurisdiction over the decisions of customary courts on matters related to fundamental human rights principles and the principles enshrined in this law.
4. Women, children, and vulnerable groups shall be provided with free legal aid services, especially during appellate proceedings before the regular first-instance court

The Federal Democratic Republic of Ethiopia
Ministry of Justice

### 30. የባህላዊ ፍርድ ቤት ውሳኔ አፈፃፀም

1. በዚህ አዋጅ መሰረት እውቅና የተሰጠው ባህላዊ ፍርድ ቤት ውሳኔ በይግባኝ እስካልታገደ ወይም እስካልተሻረ ድረስ በባለጉዳዮች ላይ የፀና ሆኖ በየትኛውም የኢትዮጵያ ክልል ተፈፃሚ ይሆናል፡፡
2. የባህላዊ ፍርድ ቤቶች የሚያስተላልፉትን ውሳኔ በፅሁፍ ማድረግ አለባቸው፡፡
3. ውሳኔውን ለመቀበልና ለመፈፀም እምቢተኛ የሆነን ባለጉዳይ ባህላዊ ፍርድ ቤቱ በባህል ህጉ መሰረት አስገዳጅ እርምጃዎችን በመውሰድ ሊያስፈፅም ይችላል፡፡

## ክፍል ስምንት
## ስለ ባህላዊ ፍርድ ቤቶች አስተዳደር ምክር ቤት መቋቋም፣ አደረጃጀትና ስልጣን

### 31. ስለ መቋቋም

1. የባህላዊ ፍርድ ቤቶች ማስተዳደር በክልልና በፌደራል ደረጃ የሚመሰረቱት የባህላዊ ፍርድ ቤቶች አስተዳደር ምክር ቤት ኃላፊነት ይሆናል፡፡
2. የተቋቋሙት የባህላዊ ፍርድ ቤቶች አስተዳደር ምክር ቤቶች የጋራ ጉባኤ ሊያካሂዱ ይችላሉ።
3. የፌደራል ባህላዊ ፍርድ ቤቶች አስተዳደር ምክር ቤት ተጠሪነት ለኢ.ፌ.ዲ.ሪ. የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ይሆናል፡፡
4. የክልል ባህላዊ ፍርድ ቤቶች አስተዳደር ምክር ቤት ተጠሪነት ለክልል ምክር ቤት ይሆናል።



### 30. Enforcement of Judgement

1. A final decision of the customary court, unless stayed or reversed on appeal, shall be binding on the parties and enforceable throughout all regions of Ethiopia.
2. Customary courts shall render their decision in writing.
3. Where a party refuses to accept and comply with the judgment, customary courts may enforce the judgment in accordance with customary laws.

## Part Eight
## Customary Courts Administration Council

### 31. Establishment

1. Administration of Customary Courts shall fall under the mandate of the Customary Courts Administration Council to be established at the Federal and Regional levels.
2. Federal and regional customary Courts Administration Councils may hold joint sessions.
3. The federal customary Courts Administration Council is accountable to the House of Peoples Representatives.
4. The Regional customary Courts Administration Council is responsible to a State Council.

### 32. የፌደራል ባህላዊ ፍርድ ቤቶች ምክር ቤት አባላት

ምክር ቤቱ የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል፡-

1. የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት............. ሰብሳቢ፣
2. የፍትህ ሚኒስትር .................. ምክትል ሰብሳቢ፣
3. የሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስትር ........................... አባል፣
4. የባህልና ስፖርት ሚኒስትር .............................. አባል፣
5. የፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽነር ጀነራል ........................ አባል፣
6. የፌዴራል የፍትህና የህግ ኢንስቲትዩት ዋና ዳይሬክተር ... አባል፣
7. የሽማግሌዎች ጉባኤ .... አባል

### 33. የፌደራል ባህላዊ ፍርድ ቤቶች ምክር ቤቱ ስልጣንና ተግባር

ምክር ቤቱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. የአዋጁን አጠቃላይ አፈፃፀም ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፣ ተገቢውን የማስተካከያ እርምጃ ይወስዳል፤
2. የባህላዊ ፍርድ ቤቶች የሚቋቋሙበትን፣ እውቅና የሚያገኙበትን መንገድ ያመቻቻል፤
3. የባህላዊ ፍርድ ቤቶች በአገልግሎት አሰጣጥና በአፈፃፀም የሚገጥማቸውን ችግር እየተከታተለ ድጋፍ ያደርጋል፤



### 32. Members of the Federal Customary Courts Administration Council

The Council has the following members

1. President of the Federal Supreme Court ...........Chair
2. Minister of Justice ......vice chair
3. Women and Social Affairs Minister .... member
4. Culture and Sports Minister .......... member
5. Federal Police Commission, Commissioner General.... member
6. Director of the Federal Justice and Legal Research Institute.....member
7. Elders Council .........member

### 33. Powers and Responsibilities of the Federal Customary Courts Administration Council

The Council shall:

1. Follow up and supervise the implementation of this law and take necessary measures of compliance.
2. Facilitate the establishment and recognition of customary courts
3. Monitor and support customary courts in addressing challenges they face during service provision and the enforcement of judgments.

4. የባህላዊ ፍርድ ቤቶች በዚህ አዋጅ በተመለከተው መሰረት ስራቸውን ማከወናወናቸውን አማካኝነት በየጊዜው ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፤
5. የባህላዊ ፍርድ ቤት ሽማግሌዎች በየጊዜው ስልጠናዎችን እንዲያገኙ ያደርጋል፤
6. ምክር ቤቱ የራሱን የውስጥ የአሰራር መመሪያ ያዘጋጃል፡፡
7. የክልል መንግስታት ሕግ የማውጣት ስልጣንን በማይጋፋ መልኩ ምክር ቤቱ በክልሎች የወጡ የባህላዊ ፍርድ ቤት ሕጎች ከዚህ የሞዴል ሕግና ከሕገ መንግስቱ መጣጣማቸውን ሊመለከተና ሊያረጋግጥ ይችላል፡፡
8. ምክር ቤቱ በባህላዊ ፍርድ ቤቶች ያለ የሰብዓዊ መብት አከባበር እና ደረጃ የሚገመገምበት መመሪያ ያዘጋጃል፡፡

## 34. የፌደራል ባህላዊ ፍርድ ቤት ምክር ቤት ጽህፈት ቤት

1. ምክር ቤቱ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ስር የሚደራጅ ጽህፈት ቤት ይኖረዋል፤
2. የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ለጽህፈት ቤቱ አስፈላጊ በጀትና የሰው ሀይል ይመድባል፤
3. ጽህፈት ቤቱ ለምክር ቤቱ የእለት ተእለት ስራዎችን ይመራል፤ የምክር ቤቱን ውሳኔዎች ያስፈፅማል፣ የሚሰጡትን ሌሎች ስራዎች ያከናውናል፡፡

4. supervise that customary courts are operating in a manner provided in this law.
5. ensure customary court judges receive regular training.
6. prepare its internal working rules.
7. without prejudice to the regional governments' law-making power, the Council may review regional customary court laws for compliance with the Model Law and the Constitution.
8. the Council shall prepare guidelines for assessing customary courts' human rights compliance and effectiveness.

## 34. Office of the Federal Customary Courts Administration Council

1. the Federal Customary Courts Administration Council shall have an office organized within the federal supreme court.
2. The federal supreme courts shall allocate the necessary budget and human resources for the office
3. the office shall lead the council's day-to-day activities, enforce its decisions and implement other activities as required.

## 35. የፌደራል ባህላዊ ፍርድ ቤቶች ምክር ቤት አባላት

ምክር ቤቱ የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል፡-

1. የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት .................. ሰብሳቢ፣
2. የክልል ፍትህ ቢሮ .....................ምክትል ሰብሳቢ፣
3. የሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ ኀላፊ.................. አባል፣
4. የባህልና ስፖርት ቢሮ ኀላፊ ..............................አባል፣
5. የክልል ፖሊስ ኮሚሽነር ጀነራል ............................ አባል፣
6. የክልል የፍትህና የህግ ኢንስቲትዩት ዋና ዳይሬክተር .......... አባል፣
7. የሽማግሌዎች ጉባኤ ........... አባል

## 36. የክልል ባህላዊ ፍርድ ቤቶች አስተዳደር ምክር ቤት ስልጣንና ተግባር

1. የክልል ባህላዊ ፍርድ ቤቶች አስተዳደር ምክር ቤት ከፌደራል አቻው ጋር በመተባበር በክልሉ ለሚገኙ ለባህላዊ ፍርድ ቤት ዳኞች የአቅም ግንባታ መመሪያዎችን ያዘጋጃል፡፡
2. የክልል ባህላዊ ፍርድ ቤቶች አስተዳደር ምክር ቤት በተወሰነ ወቅት ልዩነት የባህላዊ ፍርድ ቤቶችን አሰራርና ውጤታማነት ይገመግማል፡፡
3. የክልል ባህላዊ ፍርድ ቤቶች አስተዳደር ምክር ቤት በክልሉ የሚገኙ የባህላዊ ዳኞች መሾም፣ መሻር ወይም በገዛ ፈቃድ ከሹመት መልቀቅን በተመለከተ ስልጣን ይኖረዋል፡፡
4. ምክር ቤቱ የራሱን የውስጥ የአሰራር መመሪያ ያዘጋጃል፡፡



## 35. Members of the Regional Customary Courts Administration Council

The Council has the following members:

1. President of the Regional Supreme Court …Chair
2. Head of the Regional Justice Bureau … vice chair
3. Head of the Regional Women and Social Affairs Bureau …. member
4. Head of the Regional Culture and Sports Bureau …. member
5. Commissioner General of the Regional Police Commission, Commissioner General … member
6. Director of the Regional Justice and Legal Research Institute…member
7. Elders Council …member

## 36. Powers and Responsibilities of Regional Customary Courts Administration Council

1. Regional Customary Courts Administration Councils shall prepare capacity-building guidelines for their respective regions in cooperation with their Federal counterparts.
2. Regional Customary Courts Administration Councils shall conduct periodic compliance and effectiveness assessments of customary courts.
3. Regional Customary Courts Administration Councils shall have the power to decide on the appointment, resignation, and termination of customary court judges in their respective regions.
4. prepare its internal working rules.

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ The Federal Democratic Republic of Ethiopia የፍትህ ሚኒስቴር Ministry of Justice

## 37. የክልል ባህላዊ ፍርድ ቤቶች አስተዳደር ምክር ቤት ጽህፈት ቤት

1. ምክር ቤቱ በክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ስር የሚደራጅ ጽህፈት ቤት ይኖረዋል፤
2. የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ለጽህፈት ቤቱ አስፈላጊ በጀትና የሰው ሀይል ይመድባል፤
3. ጽህፈት ቤቱ ለምክር ቤቱ የእለት ተእለት ስራዎችን ይመራል፤ የምክር ቤቱን ውሳኔዎች ያስፈፅማል፣ የሚሰጡትን ሌሎች ስራዎች ያከናውናል፡፡

## ክፍል ዘጠኝ

## ግጭቶችን ስለመፍታትና ቅጣት

**38.** ባህላዊ ፍርድ ቤቶች የተጋጩ ወገኖችን በማስማማት ላማስታረቅ መጣር ይኖርባቸዋል።

**39.** ባህላዊ ፍርድ ቤቶች የሚጥሉት የፍታሕቤርም ሆነ የወንጀል ቅጣት በሌሎች ህጎች በመደበኛው ፍርድ ቤት እንዲጣሉ ከተደነገጉ ቅጣቶች ጋር መመሳሰል ላይኖርባቸው ይችላል።

**40.** የባህላዊ ቅጣት አፈጻጸም በበህላዊ አሰራርና ተቋማት ላይ ሊሞረከዝ ይችላል።

**41.** ባህላዊ ፍርድ ቤቶች በባህላዊ ፍርድ ቤቶች ለመደኛት ፍቃዳቸውን ሰጥተው ሆነ ብለው ከቀጥሮ በሚቀሩ ሰዎች ላይ ቅጣት ሊጥሉ ይችላሉ።

**42.** ባህላዊ ፍርድ ቤቶች የፍትሕ አሰጣት ሂደትን በሚያስተጓጉሉ፣ የፍርድ ቤት ዳኞች ወይንም ሽማግሌዎች ክብርና ደህንነት በሚያውኩ ፣ ችሎት በሚደፍሩ ሰዎች ላይ ቅጣት መጣል ይችላሉ።

**43.** ይህ አዋጅ ባህላዊ ፍርድ ቤቶች በሌሎች ሕጎች ለመደበኛ ፍርድ ቤቶች የተቀመጡ የቅጣት አይነቶችን እንደየሁኔታው እንዳይመርጡ የሚከለክል ተደርጎ ሊወሰድ አይቻልም።



## 37. Office of the Regional Customary Courts Administration Council

1. The Regional Customary Courts Administration Council shall have an office organized within the federal Supreme Court.
2. The Regional supreme courts shall allocate the necessary budget and human resources for the office.
3. The office shall lead the council's day-to-day activities, enforce its decisions and implement other activities as required.

## Part Nine

## Settlement of Dispute and Sanctions

**38.** Customary Courts shall strive to settle disputes amicably.

**39.** Customary courts are not required to adopt or impose civil or criminal sanctions provided in laws applicable by regular courts.

**40.** Enforcement of customary sanctions may rely on customary practices and institutions.

**41.** Customary courts may penalize persons who deliberately fail to appear before them after customary proceedings have started pursuant to his/her consent.

**42.** Customary courts may impose sanctions on persons involved in contempt of court, disrupting the administration of justice and violating the integrity and security of customary court judges or elders.

**43.** Nothing in this proclamation shall be construed as limiting customary courts from choosing sanctions and enforcement methods utilized by regular courts.

The Federal Democratic Republic of Ethiopia
Ministry of Justice

## ክፍል አስር
## የማሻሻያ እርምጃዎች እና ግዴታዎች

### 44. የማሻሻያ እርምጃዎች

1. የባህላዊ ፍርድ ቤቶች ዳኞች የሰብዓዊ መብት መርሆዎች እና ዋስትናዎችን በሚመለከት የአቅም ግንባታ ስልጠና ሊሰጣቸው ይገባል::
2. ሴቶች እና ለጉዳት ተጋላጭ የሆኑ ሰዎች በተለይ በይግባኝ ሰሚ ደረጃ በሚኖሩ ጉዳዮች ላይ ከክፍያ ነጻ የሕግ ድጋፍ ሊቀርብላቸው ይገባል::

### 45. የክልል መንግስታት ስልጣንና ኃላፊነት

1. የክልል መንግስታት ይህንን የሞዴል ሕግ፣ የፌደራል ሕገ መንግስቱን፣ እና የራሳቸውን ሕገ መንግስቶች እና ሕጎችን ባገናዘበ መልኩ ባህላዊ ፍርድ ቤቶችን አማራጭ የግጭት መፍቻ መንገድ አድርገው ለመመስረት ይችላሉ::
2. የክልል መንግስታት ይህን የሞዴል ሕግ ግንዛቤ ውስጥ ባስገባ መልኩ የባህላዊ ፍርድ ቤቶች የሚሰሩበትን ዝርዝር መመሪያ ወይንም ህግ ማዘጋጀት ይኖርባቸዋል::
3. የክልል መንግስታት ባህላዊ ፍርድ ቤቶች ከመመስረታቸው አስቀድሞ በክልላቸው የሚገኙትን ባህላዊ ህጎችና ተቋማትን በሚመለከት በቂ ጥናት ማድረግ ይኖርባቸዋል::
4. የክልል መንግስታት የባህላዊ ፍርድ ቤቶች ተመስርተው ወደ ስራ መግባት ከሕገ መንግስታዊ ድንጋጌዎች እና የሰብዓዊ መርሆች ጋር በተጣጣመ መልኩ መሆኑን ማረጋገጥ ይኖርባቸዋል፡
5. የክልል መንግስታት ባህላዊ ፍርድ ቤቶችን ለመመስረት የሚያዘጋጁት ረቂቅ ሕግ ላይ የፌደራል የባህላዊ ፍርድ ቤቶች አስተዳደር ምክር ቤት አስተያየቱን እንዲሰጥበት ሊጠይቁ ይችላሉ::
6. የክልል መንግስታት ባህላዊ ፍርድ ቤቶች ይህን ሞዴል ሕግ አክብረው መስራታቸውን መከታተልና መቆጣጠርን በተመለከተ ከፌደራል መንግስት ጋር መተባበር ይኖርባቸዋል::
7. የክልል ፍትህ ቢሮዎች ለሴቶች እና ለጉዳት ተጋላጭ የማህበረሰብ ክፍሎች ከክፍያ ነጻ የሚሰጥ የህግ አገልግሎት ድጋፍን በሚመለከት ከፍትህ ሚኒስቴር እና ከሌሎች

## Part Ten
## Compliance Measures and Obligations

### 44. Compliance Measures

1. Customary Court judges shall receive capacity-building training on human rights principles and guarantees.
2. Women and vulnerable groups shall receive legal aid services free of charge, in particular at the appellate levels of their proceedings.

### 45. Powers and Responsibilities of Regional Governments

1. Regional Government may, in line with this Model law, the Federal Constitution, and their respective regional constitutions and laws, establish customary courts to serve as alternative avenues for dispute resolution.
2. Regional governments shall provide detailed guidelines or laws for the operation of customary courts in line with this Model Law.
3. Regional governments shall undertake appropriate studies on the nature of specific customary laws and institutions prior to establishing customary courts.
4. Regional governments shall ensure that the establishment and operation of customary courts are compliant with the Constitution and Human Rights principles.
5. Regional Government may request the Federal Customary Court Administration Council to review and comment on draft laws for the establishment of customary courts.
6. Regional governments shall cooperate with the federal government in supervision and monitoring customary courts' compliance with this Model Law and the Constitution.
7. Regional Bureau of Justice shall cooperate with the Ministry of Justice and other stakeholders in

The Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Justice

ለድርሻ አካላት ጋር በትብብር መስራት ይኖርባቸዋል፡፡

8. የክልል መንግስታት እስከ ታች መዋቅር ያሉ የአስተዳደር እርከኖች ላይ የባህላዊ ፍርድ ቤቶች ውሳኔዎችን የሚያስፈጽሙ ጽ/ቤቶችን በህግ መወሰንን ጨምሮ የባህላዊ ፍርድ ቤቶች የተቀላጠፈ አሰራር መኖርን ያረጋግጣሉ፡፡

**46. የፌደራል መንግስት ስልጣንና ኃላፊነት**

1. ከላይ በአንቀጽ 22 ላይ የተደነገገውን በሚመለከት በመደበኛ ፍርድ ቤቶች የሚደረግ የወንጀል ክስ ሂደት የማስቀረት ወይም የማቋረጥ ስልጣን የፌደራል መንግስት ይሆናል፡፡
2. ለህዝብና ፍትሕ ጥቅም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የፌደራል መንግስት በባህላዊ ፍርድ ቤቶች የተያዘን የእርቅ ጉዳይ ይከታተላል፡፡
3. የፍትህ ሚኒስቴር እና ሌሎች የሚመለከታቸው የፌደራል መንግስት ተቋማት በባህላዊ ፍርድ ቤቶች የሚታዩ ጉዳዮችን በሚመለከት ለሴቶች እና ለጉዳት ተጋላጭ የማህበረሰብ ክፍሎች ከክፍያ ነጻ የሚሰጥ የህግ አገልግሎት ድጋፍን ማበረታታት ይኖርባቸዋል፡፡
4. የፍትህ ሚኒስቴር ከክልል የፍትህ ቢሮዎች ጋር በመተባበር ከክፍያ ነጻ የሚሰጡ የሕግ አገልግሎቶች ከባህላዊ ፍርድ ቤቶች የቀረቡ ጉዳዮችንም እንደሚያካትቱ ማረጋገጥ ይኖርባቸዋል፡፡
5. የፌደራል ፖሊስና የማረሚያ ቤቶች አስተዳደር ባህላዊ ፍርድ ቤቶች በህግ የተሰጣቸውን የዳኝነት ስልጣን በሚተገብሩበት ወቅት መተባበር ይኖርባቸዋል፡፡
6. በጉዳዩ ላይ ባህላዊ የፍትሕ ሂደት ከተጀመረ ፖሊስ በደንብ መተላለፍ ወይንም በዐቤቱታ ብቻ ከሚከሰሱ ወንጀሎች ጋር በተገነኘ በቁጥጥሩ ስር ያሉ ሰዎችን ወድያውኑ መልቀቅ አለበት።

ensuring the provision of free legal aid services to women and vulnerable groups of society.

8. Regional governments shall guarantee the smooth operation of customary courts, including designating by law local and district-level offices responsible for the enforcement of decisions and sanctions of the Customary Courts.

**46. Powers and Responsibilities of the Federal Government**

1. With respect to Article 22, the federal government has the power to decide not to pursue criminal accountability using the regular courts.
2. The Ministry of Justice may observe reconciliation proceedings by customary courts when deemed necessary in the interest of justice.
3. The Ministry of Justice and other relevant federal government institutions shall encourage the provision of legal aid services to assist women and other vulnerable groups in their appeals from customary courts to regular first-instance courts.
4. The Ministry of Justice shall, together with regional Justice Bureaus, ensure that pro bono legal service includes cases before customary courts.
5. The Federal Police and Prison Administration Officials shall cooperate with customary courts in the exercise of their jurisdiction.
6. As regards petty offences and offences punishable only upon complaint, the federal police shall immediately release from its custody a person against whom there is a proceeding before customary courts.

## ክፍል አስራ አንድ
## ከሌሎች ፍርድ ቤቶች ጋር የሚኖር ግንኙነት

**47. ከመደበኛ ፍርድ ቤቶች ጋር የሚኖር ግንኙነት**

1. መደበኛ ፍርድ ቤቶች አለመግባባቶች በባህላዊ ፍርድ ቤቶች እንዲፈቱ ሊያበረታቱ ይችላሉ፡፡
2. መደበኛ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤቶች በይግባኝ ሰሚ ባህላዊ ፍርድ ቤቶች በተሰጠ ውሳኔ ላይ የመጨረሻ የይግባኝ ዳኝነት ስልጣን አላቸው፡፡
3. መደበኛ ፍርድ ቤቶች በባህላዊ ፍርድ ቤቶች በተላለፉ ውሳኔዎች ላይ የሚኖራቸው ስልጣን ርዕትዕን እና ፍትሀዊነትን በሚመለከት እና የህገ መንግስታዊ ወይም የሰብዓዊ መብት መርሆችን ማስከበርን በሚመለከቱ ጉዳዮች የተወሰነ ይሆናል፡፡
4. መደበኛ ፍርድ ቤቶች ተከራካሪ ወገኖች ጉዳያቸው በባህላዊ ፍርድ ቤቶች ቢታይላቸው ፈቃደኛ እንደሚሆኑ ሊጠይቁ ይችላሉ፡፡
5. በተከራካሪ ወገኖች ፈቃድ በግልግል ሊፈቱ የሚችሉ ጉዳዮችን መደበኛ ፍርድ ቤቶች ወደ ባህላዊ ፍርድ ቤቶች ሊመሩ ይችላሉ፡፡
6. በመደበኛ ፍርድ ቤቶች ብቻ ሊታዩ የሚችሉ የወንጀል ክስ ሂደቶችን በሚመለከት መደበኛ ፍርድ ቤቶች በባህላዊ ፍርድ ቤቶች የሚፈጸሙ የዕርቅ ሂደቶች ጥቅሞችን ማስረዳት ይጠበቅባቸዋል፡፡

**48. ከሀይማኖታዊ ፍርድ ቤቶች ጋር የሚኖር ግንኙነት**

1. ባህላዊ ፍርድ ቤቶች በሀይማኖታዊ ፍርድ ቤቶች የተያዙ ጉዳዮችን የመዳኘት ስልጣን አይኖራቸውም፡፡
2. ባህላዊ ፍርድ ቤቶች በሀይማኖታዊ ፍርድ ቤቶች ብቻ ሊዳኙ የሚችሉ ጉዳዮችን የመዳኘት ስልጣን አይኖራቸውም፡፡
3. ሀይማኖታዊ ፍርድ ቤቶች በባህላዊ ፍርድ ቤቶች የዳኝነት ስልጣን ስር የተቀመጡ ጉዳዮችን የመዳኘት ስልጣን አይኖራቸውም፡፡



## Part Eleven
## Relationship with other courts

**47. Relationship with Regular Courts**

1. Regular courts may encourage the resolution of disputes by customary courts.
2. First Instance Regular Courts may have a last resort jurisdiction over cases adjudicated by Appellate Customary Courts.
3. The jurisdiction of regular courts over the decisions of customary courts shall be limited to issues of equity and fairness as well as questions concerning the compliance of customary decisions with the Constitution and human rights law.
4. Regular Courts shall inquire with the parties if they prefer to take their cases before the Customary Courts.
5. With the consent of the parties, Regular Courts may refer proceedings to customary courts in cases requiring settlement of disputes through arbitration.
6. For criminal cases under their exclusive jurisdiction, regular courts shall explain the advantages of reconciliatory proceedings by customary courts.

**48. Relationship with Religious Courts**

1. Customary Courts shall not entertain cases pending before religious courts
2. Customary courts shall not see cases falling exclusively under the jurisdiction of religious courts.
3. Religious courts shall not adjudicate cases that exclusively fall under the jurisdiction of customary courts.

## ክፍል አስራ ሁለት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 49. የመተባበር ግዴታ

ማንኛውም ሰው የባህላዊ ፍርድ ቤት ጥያቄ፣ ትእዛዝ እና ውሳኔ መፈጸም አስፈላጊውን ህጋዊ ትብብር የማድረግ ግዴታ አለበት፡፡

### 50. ስለ ተጠያቂነት

ባህላዊ ፍርድ ቤቱ የመተባበር ግዴታውን በማያከብር ባለጉዳይ ወገን ላይ በባህል ህጉ መሰረት ተገቢውን እርምጃ ይወስዳል፡፡ ሆኖም እርምጃው እስርን ማካተት የለበትም፡፡

### 51. ተፈጻሚነት የሌላቸው ሕጎች

ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረን ማናቸውም አዋጅ፣ ደንብ፣ መመሪያ፣ የአሠራር ልምድ ወይም ውሳኔ በዚህ አዋጅ በተመለከቱ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡

## Part Twelve

## Miscellaneous Provisions

### 49. Duty to Cooperate

Any person shall cooperate in the execution of requests, decisions, or orders issued by customary courts.

### 50. Accountability

The customary court shall take measures in accordance with customary rules against any person who fails to discharge his obligation to cooperate with the court. Nonetheless, such a measure shall not include imprisonment.

### 51. Inapplicable Laws

Any proclamation, regulation, directive or decision inconsistent with this proclamation shall be inapplicable concerning matters provided for in this Proclamation

---

The Federal Democratic Republic of Ethiopia
Ministry of Justice